Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# ሆሳዕና፡ ከትንሽ ወታደራዊ ካምፕነት በሬሚታንስ ወደ ጎመራች የኢኮኖሚ ማዕከልነት

የሰላም ምርምር ተቋም/ሪፍት ቫሊ ኢንስቲትዩት፣ በኢትዮጵያ የሚታዩ የከተማ ውዝግቦች ጥናት ፕሮጀክት

**የካቲት 2017**

## ማጠቃለያ

ይህ ጽሑፍ አዲስ በተቋቋመው የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ውስጥ በሀዲያ ዞን በምትገኘው ሆሳዕና ከተማ ለሀብት ባለቤትነት እና ቁጥጥር የሚደረግ ውዝግብ ላይ የተደረገ ጥናት ሪፖርት ነው።

ጥናቱ የከተማዋን መስፋፋት ተከትሎ በቀድሞ በተወሰኑ ቡድኖች ተይዞ የነበረው የማኅበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ኃይል ተገለው በነበሩ የአካባቢው ተውላጆች መተካቱን በማሳየት፣ የሀዲያ ተወላጆች ወደ ደቡብ አፍሪካ የሚያደርጉት ፍልሰት በእነዚህ አዳዲስ ለውጦች ላይ ያሳድርውን ሚና የሚያስስ ነው።

በሆሳዕና የሚታዩት ዋነኛ የውዝግብ ምንጮች በብሔሩ (በሀዲያ ማኅበረሰብ ውስጥ) የሚታዩ እና በኃይማኖቶች መካከል ያሉ ልዩነቶች ናቸው። ምንም እንኳን እነዚህ አለመግባባቶች ከባድ ቢሆኑም፣ በአብዛኛው በኃይል የተደገፉ ባለመሆናቸው፣ በአንጻሩ ተመሳሳይ አለመግባባቶች ሲኖሩ ከባድ ግጭት ከሚያጋጥማቸው ከተሞች ለየት ይላል። ጥናቱ ከሆሳዕና ከተማ መስፋፋት ጋር የተቆራኙ አራት ተያያዥነት ያላቸውን የውዝግብ መንስዔዎችን ተመልክቷል፦

**1. የከተማ ለውጥ ውጥረቶች፦** ይህ በዋነኛነት ውጭ አገር ኖረው በመሥራት ራሳቸውን በለወጡ አዳዲስ የሀዲያ ባለ ሀብቶች ሐዲያ ካልሆኑ የሆሳዕና ነዋሪዎች በመሀል ከተማ የመኖሪያ ቤቶችን መግዛታቸው ከታሪካዊ ነባራዊ ሁኔታ በተገላቢጦሽ ሻጮቹ ወደ ከተማው ጫፍ እንዲወጡ ያደረጋቸው አዝማሚያ ነው።

**2. በከተማ ዳርቻ የሚስተዋሉ የመሬት ግጭቶች**፡ ሕገ መንግሥቱ የመሬት ባለቤትነትን ለኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ስለሚደነግግ፣ ለግለሰቦች በመሬት የመገልገል መብትን ብቻ ይሰጣል። ፈጣን የከተማ

መስፋፋት በከተማ ዙሪያ ያሉ ማኅበረሰቦችን በተደጋጋሚ አደጋ ላይ በመጣሉ፣ ወደ ኢ-መደበኛ አሰፋፈር እንዲገቡ ያስገድዳቸዋል። በሆሳዕና ዙሪያ ባሉ አካባቢዎች ላይ በዲያስፖራው የሚደረገው ኢንቨስትመንት በሌሞ ወረዳ የሚኖሩ እና በሌሎች የሀዲያ ጎሳዎች መካከል አለመግባባት እንዲፈጠር አስተዋፅዖ አድርጓል። በከተሞች መስፋፋት ምክንያት ከገጠር ወደ ከተማ የሚደረገው ፍልሰት፣ የሌሞ አርሶ አደሮች መሬታቸውን አንድም በውዴታ ሌላው ደግሞ ከመንግሥት ሽንሽና ለማትረፍ በሚል ሳይወዱ እንዲሸጡ ከፍተኛ ጫና አሳድሮባቸዋል። ይህ ሁኔታ እነዚህን አርሶ አደሮች በማደኅየት ከመሬት ገዥዎች ጋር እንዲጋጩ እያደረገ ይገኛል። የኢትዮጵያ የከተሞች ልማት ስትራቴጂ አተገባበር የከተማ መሬትን በመንግሥት አማካይነት በግዴታ በመውሰድ ላይ የተመሠረተ በመሆኑ፣ አርሶ አደሮች ከነንብረታቸው ለልማት በሚል ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። ይሁን እንጂ፣ ከዚህ በተለየ በሆሳዕና ከተማ ጫፎች ላይ ብዙም ጉልህ የሆነ መስፋፋት አልታየም። ይልቁንም መደበኛ ያልሆነ የመሬት ገበያ በመፈጠሩ፣ የሀዲያ አርሶ አደሮች መሬታቸውን ከደቡብ አፍሪካ ለሚመለሱ ዲያስፖራዎች እየሸጡ ይገኛሉ። ይህ ኢ-ፍትሐዊ የንግድ ልውውጥ እና ዕቅድ አልባው የከተማ ማስፋፊያ ሥራ ወደ አጎራባቹ የሌሞ ወረዳ በመስፋፋት ብዙ አርሶ አደሮችን መሬት አልባ አድርጓቸዋል።

**3. የሕዝብ መሰብሰቢያ ቦታና የባህል ፍልሚያ፡-** እንደ አዲስ እየተነቃቃ የሚገኘው የሀዲያ ባህላዊ ልምምድ ከፕሮቴስታንት እና ከኦርቶዶክስ ክርስትያን ትውፊቶች ጋር በሚጋጭ መልኩ የአደባባዮች አጠቃቀም ውዝግብን እየፈጠረ ይገኛል። ለሀዲያ ማንነት ዋነኛ መድረክ ሆኖ የሚያገለግለው አዲሱ የባህልና ትውፊት ማንሰራራት በርካታ ውዝግቦችን ፈጥሯል። ይህም በዋነኝነት ጎፈር ሜዳን ሀዲያ ናፋራ (የሀዲያ በራፍ) በሚል ስም ተቀይሮ ያሆዴን በተለያዩ ይዘቶች ማክበር በመጀመሩ እንደዚህ ያሉ የአደባባይ በዓላት በሚከበሩበት ስፍራዎች ላይ መጠነኛ ግጭቶች ተስተውለዋል።

**4. የክልል ዋና ከተማነት ፍልሚያ፡-** ለማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልላዊ መንግሥት ዋና ከተማነት የሚደረገው ፉክክር በዋናነት በሀዲያ እና በጉራጌ ዞኖች መካከል ሲሆን፣ አሁን ያለው የመድብለ ከተማ አካሄድ ሆሳዕናን የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር መቀመጫ፣ ወልቂጤን ደግሞ የክልሉ ምክር ቤት መቀመጫ አድርጎ በመሰየም በሁለቱ ዞኖች መካከል ያለውን ፍትጊያ ለመቀነስ ያለመ ነው። በሆሳዕና በኩል የሚነሳው የክልል ዋና ከተማነት ፍላጎት፣ የታላቋን ሀዲያ ፕሮጀክትንጨምሮ አዳዲስ የፖለቲካ ፍላጎቶችን ቀስቅሷል። ይህም ከሀዲያ ሱልጣኔት ጀምሮ የነበሩ ግዛቶችን ለማስመለስ ያለመ ሲሆን፣ ከጉራጌ ብሔርተኞች ጋር በክልላዊ ወሰን ዙርያ ግጭቶች እንዲፈጠሩ አድርጓል።

## የኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም

ይህ ሪፖርት ለኢትዮጵያ የሰላም ምርምር ተቋም የተጻፈ ሲሆን፥ ውዝግብ የሚታይባቸው የከተማ ስፍራዎችን የተመለከቱ ጭብጦች የተዳሰሱበት የዕውቀት ለሰላም (Knowledge for Peace) ምርምሮች አካል ነው። የሰላም ምርምር ተቋም ገለልተኛ የሆነ ወቅታዊ የሰላምና የግጭት ትንታኔዎችን ከኢትዮጵያዊ ባለሙያዎችና ተመራማሪዎች በማቀናጀት በአገሪቱ ግጭት አገናዛቢ የሆነ የፖሊሲና ፕሮግራም ቀረጻ እንዲኖር ያግዛል። ተቋሙ በሪፍት ቫሊ ኢንስቲትዩት (አር ቪ አይ) የሚተዳደር ሲሆን፥ በእንግሊዝ መንግሥት ድጋፍ ይደረግለታል።

## የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም

የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም በምስራቅና ማዕከላዊ አፍሪካ የሚሠራ ሲሆን፣ አገር በቀል ዕውቀቶች በማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ልማት ላይ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው ማድረግ ነው። የቅጂ መብት © የስምጥ ሸለቆ የጥናት ተቋም 2017። ይህ ሪፖርት በክሪኤቲቭ ኮመንስ አሠራር መሠረት ለንግድ ላልሆነ ዓላማ ይዘቱ ሳይቀየር መጠቀም እንዲቻል ተፈቅዶ የታተመ ነው (CC BY-NC-ND 4.0)።

Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility